# የዝቋላ ተራራ ትዝታ…

ገ/ኢ.ጐርፉ

የዝቋላ ተራራ ከአዲስ አበባ ከተማ በስተደቡብ ሓምሳ ኪሎ ሜትር እንኳን በማይሞላ ርቀት የሚገኝ፣ ከስዕሉ እንደሚታየውም በአዲስ አበባ ከተማና በተራራው መካከል ያለው ፊት ለፊት ለጥ ያለ የአድኣ ወረዳ ሜዳ ነው።



ከዚህ ቀጥሎ የምተቸው በግምት ከዓርባ ዓመት በፊት ወጣት፣ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሆኜ፣ በእግሬ ዝቋላ ለጉብኝት ተጉዤ፣ ያየሁትና የተመለከትኩት ነው።

ዛሬ ሁኔታው ብዙ መለወጡን አላውቅም፣ ተለውጦም ከሆነ በቅርብ ጊዜ ያዩት አንባቢዎች፣ አስተያየታቸውና ምን ያህልስ ለውጥ መኖሩ ቢጽፉ ደግ ነው።

ከተራራው ፊት ለፊት የሚታየው የአድኣ ሜዳ በክረምትና በበልግ ወራት በብዙ ልምላሜ፣ በታወቀው የአድኣ ማኛና ሰርገኛ ጤፍ፣ በብዙ ሌላም አዝርእት ይልብሳል። በበጋ ግን ደረቅና የውሃ ችግር በጣም የሚያጠቃው ቦታ ነው። ኗሪዎቹ በማለዳ ከሩቅ ተጉዘው፣ የተገኘውን የውሃ ጥርቃሚ ኩሬ፣ ጐርፍ ያመጣውን ወራጅ በትንሽ ጎድጓዳና ረባዳ ቦታ ተከማችቶ፣ በእሾኽ ኣጥር የተከተረውን ውሃ ቀድተው፣ በአህዮችና በሌላም ከብቶች ጭነው ወደየቤታቸው ውስደው ለየዕለቱ የሚያስፈልጋቸውን ይጠቀማሉ።

ኩሬውና የተከተረው ውሃ ግን ኣገልግሎቱ ለሰው ብቻ ሳይሆን ለከብትም፣ ለሰማይ አዕዋፍና ለሜዳ አውሬም በመሆኑ፣ ከብቶቹም ከዚያው ጠጥተው ከዚያው ስለሚጸዱ፣ ውሃው በጣም ቆሻሻና ለጤናም እጅግ ኣደገኛ ነው። ግን ሌላ ከየት ይምጣ! ስለዚህም ውሀ የጠማን መንገደኞች ስንለምናቸው፤ “ቢሻን እንጅሩ” ማለትን እንጂ ውሃ የሚሰጥ እምብዛም የለም ነበር።

በደረቀ ወንዛወንዝና የከብት እግር ባወጣው ጐርባጣ-ጎጥ መንገድም ጂፕና ላንድሮቨር የሚሄዱበት፣ ከዱከምና ከደብረዘይት አንስቶ እስከ ተራራው፣ ዝቋላ ጫፍ ድረስ የሚወስድ፣ የኣፈርና የኣሸዋ መንገድ አለ። ግን ያበደ ሾፌር ካልሆነ ማን ይሄድበታል! ስንሄድም፣ ስንመለስም መንገዱ ባዶውን ኣየን እንጂ ኣንዲትስ መኪና የሚባል ሲጓዝበት ፈጽሞ አላየንም።

ወደ ተራራው አካባቢ ስንጠጋም ጫካው ጥቅጥቅ እያለ፣ በታላላቅ ዛፎች፣ በዝግባና ደድሆ፣ ወይባና ቀጋ፣ ወይራና የኮሶም ዛፎች እየለበሰ መጣ። በተለይ ከኮሶ ዞፍ ላይ ያለው ብጫና ቀይ የሚያምር አበባና ፍሬው ከሩቁ ሆኖ በነፋሱ ወዲህና ወድያ ሲወዛወዝ ማየቱ እጅግ ደስ የሚል ነበር።

መንገዱን የጀመርነው በማለዳ ሲሆን ወደ ተራራው ዙርያ የተጠጋን ፀሓይ መራራ ሆና ወደ ተሲያት አካባቢ ነበር። ታድያ የሚያውቅ መሪ ካልያዙ ተራራውን መውጣት ቀላል አይደለም። ገደላ-ገደልና ጥቅጥቅ ያለ ዱርም ስለሆነ፣ አንዱን የከብት ወይም የጠጣ መንገድ ተከትሎ ቢኬድ፣ የጠጣ መንገድ ገደል ያደርሳል እንዲሉ፣ ከገደል አፋፍ ደርሶ ቀጥ ማለት ነው።

ደግነቱ አጋጣሚ ሆኖ አንድ መንገደኛ መነኩሴ ኣግኝተውን፣ እሳቸውም ከተራራው ጫፍ ወደሚገኝ የአቦ ገበረ-መንፈስ ቅዱስ ገዳም ተጓዥ ስለ ነበሩና፣ መንገዱንም ሄደውበት ኖረው በመጠኑ ስለሚያውቁት፣ እየመሩን ተራራውን ተያያዝነው። ያም ሆኖ ካንዴም ሁለቴ መንገዱን ለቅቀው በመሳታቸው ከገደል አፋፍ ደርሰን ለመመለስ መገደዳችንን ኣልረሳውም።

ከተራራው ጫፍ ስንደርስ ፀሓይ ወደመጥለቋ ገደማ ሆኖ፣ ለዓይን መያዝ ጀምሯል። ይሁንና የቤተክርስትያኑን ኣካባቢ ጐብኝተን ከተራራው ላይ ያለውንም ኩሬ ተመለከትን። ይህ ኩሬ መጠኑ ትልቅ ባይሆንም በዓለም በከፍተኛነት ቦታ ላይ ካሉት ኩሬዎች ኣንዱ እንደሚሆን ኣያጠራጥርም። ምክንያቱም የኣዲስ ኣበባ ከተማ ከባሕር በሰባት ሺሕ ጫማ ላይ ስትገኝ፣ ተራራውም በግምት ከዚያ ወደሦስትና ኣራት ሺሕ ጫማ ከፍ ስለሚል፣ ኩሬው በትንሹ ከዓስር ሺሕ ጫማ ከፍታ በላይ ይገኛል ማለት ነው።

በኩሬው ዙርያም ብዙ ታላላቅ ዛፎች ይገኛሉ፣ በዛፎቹም ብዙ ጦጣዎችና ጉሬዛዎች ከቅርንጫፍ ወደ ቅርንጫፍ እየዘለሉ ውር፣ ውር ይሉ ነበር። ከኩሬው በስተደቡብ/ምስራቅም ኣንድ ትልቅ የደንጊያና የኣፈር ክምር ኣለ። የዚህም የዲንጋይ ክምር ድንቅ ምስጢር በማግሥቱ ነው የሰማነው።

ምሽቱን - ለካስ ዕለቱ የኣቦ ገብረመንፈስ ቅዱስ ታቦት የሚከበርበት ዕለት ኖሯል፣ ቀን ከገዳሙ ትልቅ ድግስ ውሏል ኣሉን - መነኩሳቱና ካህናቱም “ምግብ ቀርቧል!” ብለው መኣድ ኣስቀመጡን፣ ማለፊያ የሆነ እራትም ኣቀረቡልን። እንጀራም፣ ወጥም፣ ጥሬ ስጋም፣ ጠላም፣ ምንም የቀረ የለም፣ በልተን፣ ጠጥተን ጠገብን። ከዚያም ለመኝታችን ተዘጋጀን…

በኢትዮጵያ ክፍለ-ሃገራት ስዞር የዚህ ዓይነቱ የነፃ ድግስ በብዙ ተደጋግሞ ኣጋጥሞኛል፣ ይህንም ሳስታውስ፤ “ለዚህ ለየዋሁ ወገኔ፣ ላበላኝ፣ ላጠጣኝ፣ ምን ኣደረግኹለት!” እያልኩ፣ ሁሌ የሚያሳስበኝ ጉዳይ ነው። ይቀጥላል…